5 DISC INSERT

# በስርዓት የሚሄድ ትውልድ

አዲስ ኪዳን ስለ ብሉይ ኪዳን መጻህፍት ሲናገር ሁሉ ስለ ትምህርታቸው ተጻፈ ይላል:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበሩ አባቶች ስህተታቸው፣ የልባቸው ሃሳብ፣ ከስህተት በኋላ የወሰዱት እርምጃ፣ ብሎም የእግዚአብሔር ምላሽ በግልጽ ተቀምጦአል:: የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉስ ሳኦል ከሞተ በኋላ ስለ ዘመኑ  መጽሐፍ ሲናገር በአንድ ዓረፍተ ነገር ጠቅልሎ እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል:: "ሳኦል እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ ሞተ" በሌላ በኩል ደግሞ እርሱን ተከትሎ ንጉስ ስለሆነው ዳዊት መጽሓፍ ሲናገር "ዳዊት በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ" ይላል:: በዚህ ትምህርት ውስጥ የምታገኟቸው የዳዊትና የሳኦል በዘመናቸው፣ የመሩት ህዝብ፣ ልጆቻቸው፣  ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ህብረት፣ ድክመታቸው፣ እንዲሁም ብርታታቸው ተነጻጽረው ተቀምጠዋል::

በዘመናችን ለምናየውና ለምንሰማው እንደ ዘመኑ መሳፍንት ላለው ዝብርቅርቅ ሁኔታ እነዚህ ሰዎችና በዙሪያቸው ያሉት ሰዎች የኖሩትን ኑሮ የሚያስተካክል፣ የሚገስጽ፣ የሚያነቃ ደግሞም የሚመራ ምክር ይገኝበታል:: በህይወታችን ውስጥ እያለፉ ካሉት ነገሮች ምን ያህሉ የሚያልፈው መርሖን ከመከተላችን ወይም ከመጣሳችን ጋር ምን ያህል እንደሚያያዝ ይሄን ትምህርት ተጠቅመን እራሳችንን እንድናይ እንድንመረምር ይረዳናል:: የእግዚአብሔር ሃሳብ ላይ በፍጥነት የሚያደርስን አውራ ጎዳናው በስርዓት መኖር ነው:: ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምንጠብቃቸው ነገሮች መልስን የምናገኘው በስሜት ሳይሆን በስርዓት በመኖር ነው:: ይህ ስርዓት ግን ወደ እግዚአብሔር የማያደርሰው እና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የማይረዳው ሰው ሰራሽ ስርዓት አይደለም::

በእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች ውስጥ ያሉት መመሪያዎች የወጡት በሳኦልና በዳዊት ዘመን ከተከናወኑት ታሪኮች ውስጥ ነው:: በዚህ ትምህርት ውስጥ የሚከተሉት ሃሳቦች በጥቂቱ ተዳስሰዋል፣ ሳኦል የነገሰበት ጊዜ፣ የሳኦል ልብና አመራር፣ እግዚአብሔር ሲለየው ስለተለዩት ነገሮች እንዲሁም ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ተምኔትን እናያለን::ቀጥሎ በነገሰው ንጉስ ዳዊት እንዴት በስርዓት ሄዶ የቅባት ሙላት ላይ እንደደረሰ፣ የዳዊት ልብና አመራር፣ ኢዮአብ የዳዊትን ስልጣን መናቁ፣ የአቤሴሎምና የሳቤኤ አመጽ፣ የአዶንያስ ግብግብ እና የሰሎሞን መንገስ እንመለከታለን::



ይህ መልዕክት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ እንዲሁም ለሚያውቋቸው ሁሉ ታላቅ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚያመጣ ስለሆነ ረጋ ብለው ቢያዳምጡትና ደጋግመው ቢሰሙት እንደሚጠቀሙበት የጌታም መንፈስ የቃሉን ፍቺ እንደሚያበራልዎ በመተማመን ምንም ዓይነት ጥያቄና አስተያየት ቢኖርዎት በስልክ ቁጥር (651) 772-0216 ወይንም በአድራሻችን ቢጽፉልን ይደርሰናል::

ሜኔሶታ በምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ምክትል መጋቢ
መጋቢ እስጢፋኖስ አለሙ 2009


**አድራሻችን**
Ethiopian Evangelical Church In Minnesota ◆ 770 7th st. East ◆ St.Paul, MN 55106
(651) 772 0216 ◆ www.eecmn.org


በስርዓት የሚሄድ ትውልድ በፓስተር እስጢፋኖስ አለሙ

# በስርዓት የሚሄድ ትውልድ



በፓስተር እስጢፋኖስ አለሙ
5 CDs